# ፍርድና በፍርድ ላይ የቀረበ ትችት፡- የክልል ፍ/ቤቶች የውክልና የዳኝነት ሥልጣንና ውክልናው ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ፤

ሞላ መንግስቱ*

## መግቢያ

በዚህ ርዕስ ትችት የሚቀርበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 20465 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው። ለትችቱ ምክንያት የሆነውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በክልል ቢቋቋምም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በውክልና ሥልጣናቸው የወሰኑትን የፌዴራል ጉዳይ በይግባኝ ተቀብሎ የማየት ሥልጣኑን የሚያስቀር አይሆንም በማለት የሰበር ችሎቱ የሰጠው ድምዳሜ ነው። ይህን ድምዳሜ ለመተቸት መሠረት ተደርገው የሚጠቀሱት ደግሞ የፌዴራሉ ሕገመንግሥትና ፍ/ቤቶችን ያቋቋመው አዋጅ አግባብ ያላቸው አንቀጾች ናቸው።

በኢትዮጵያ የተመሠረተው የፌዴራል ሥርዓት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 50 የፌዴራልና የክልል የመንግሥት አካላትን የሚያቋቁም ሲሆን የመንግሥት ሥልጣንንም ለእነዚሁ አካላት በአንቀጽ 51-52 አከፋፍሎ ደንግጓል። የዳኝነት ሥርዓቱም ይህንኑ የመንግሥት አወቃቀር በመከተል በፌዴራልና በክልል ተለያይቶ የተዋቀረ በመሆኑ የፌዴራል ሥልጣን የሆኑ ጉዳዮች የሚታዩት በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሲሆን የክልል ሥልጣን የሆኑ ጉዳዮች ደግሞ የሚታዩት በክልል ፍ/ቤቶች እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል። ይሁን እንጂ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን የሆኑ ጉዳዮች በክልሎች የዳኝነት ጥያቄ በሚነሳባቸው ጊዜ የፌዴራል ፍ/ቤቶች በክልሎች እስኪቋቋሙ ድረስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሥልጣን ለክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን ደግሞ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በውክልና የተሰጠ መሆኑን የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 80 ደንግጓል።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች በአገሪቱ በሞላ ወይም በተወሰኑ ክልሎች እንዲቋቋሙ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሊወሰን እንደሚችልም እንደዚሁ በሕገመንግሥቱ ተደንግጎ እናገኛለን። በዚህ መሠረትም ሕገመንግሥቱ ከታወጀበት ከነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ የሁሉም ክልሎች ፍ/ቤቶች ከክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው በተጨማሪ በሕገመንግሥቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት የፌዴራል ጉዳዮችንም በዳኝነት እያዩ ውሳኔ ሲሰጡ ቆይተዋል። ይሁን እንጅ መጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 322/1995 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ለማቋቋም በመውጣቱ[1] አዋጁ በክልል ፍ/ቤቶች

*ሌክቸረር አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ሕግ ት/ቤት(LL.B.,M.A.,LL.M.)፣ E-mail: mollamengt@yahoo.com.

[1] በዚህ አዋጅ በቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሱማሌና በደቡብ ብብሕ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ተቋቁመዋል።

የውክልና የዳኝነት ሥልጣን ላይ የሚያስከትለው ለውጥ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። የጥያቄውን መነሳት የበለጠ አስፈላጊና አግባብ የሚያደርገውም በክልሎቹ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሳይቋቋም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብቻ በመቋቋሙ ውክልናው በከፊል ተነስቶ በከፊል ግን እንደፀና የሚቆይበት ሁኔታ በመኖሩ የተነሳውንና እንደፀና የሚቆየውን የውክልና ሥልጣን ለይቶ ለመረዳት የሚያስቸግሩ አከራካሪ ጉዳዮች ስለሚኖሩ ነው። ይህ አሁን የሚተቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔም የዚህ ዓይነቱ አከራካሪ ጉዳይ መፈታት ያለበትን መንገድ የሚያስረዳ ሲሆን ትችቱ ደግሞ የፍ/ቤቱ አቋም ከሕገመንግሥቱ አግባብ ያላቸው አንቀጾች አንፃር አንዳንድ ግድፈቶች አሉበት የሚል ነው።

## 1. የጉዳዩ ዝርዝር

ህፃን ተመስገን ቴጂ በመኪና ተገጭቶ በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት ካሣ እንዲከፈለው በጉዳት አድራሽና ጉዳት ባደረሰው ንብረት ባለቤት ላይ የተጉጂው ህፃን ሞግዚትና አሳዳሪ አቶ ፀሐየ ዮሐንስ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ለአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ያቀርባሉ። በዚህ በከሳሽና በተከሳሾች መካከል በሚካሄደው የካሣ ክርክር አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጣልቃ ገብቶ ተከራከረ።

ክሱ የቀረበለት የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተከሳሾችም ሆነ ጣልቃ ገቡ ኢንሹራንስ ኩባንያ ለጉዳቱ ኃላፊነት እንዳለባቸው በመጥቀስ ህፃን ተመስገን ቴጂ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ ወሰነ።

አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታውን በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ለተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቀረበ። ጣልቃ ገብ ሆኖ የተከራከረው ኢንሹራንስ ኩባንያ የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረብ ፋንታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ኩባንያው በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(6) መሠረት ጉዳዩ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ነው፤ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ ሊያይ የቻለውም የፍዴራል ጉዳዮችን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ተክቶ መወሰን እንዲችል በተሰጠው የዉክልና ሥልጣን መሠረት ስለሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ሊያየው የሚገባው በክልሉ የተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው በሚል ነው።

ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ፍ/ቤትም የቀረበውን ጉዳይ ተመልክቶ ለመወሰን የሚያስችለው የሥረነገር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚል ጭብጥ ከመሠረተ በኋላ ይግባኝ ያቀረበው ኢንሹራንስ ኩባንያ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ነዋሪ በሆኑት ከሳሽና ተከሣሽ መካከል በተጀመረው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳት አድርሷል ለተባለው መኪና የመድን ሽፋን በመስጠቱ የተነሳ በመኪናው ባለቤት እግር ተተክቶ ጣልቃ ገብቶ ከመከራከሩ በስተቀር የራሱን መብትና ግዴታ

በተመለከተ የቀረበበት ክስ ስላልነበረ ክሱ የፌዴራል ጉዳይን የሚመለከት አይሆንም፤ ስለዚህም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የሥረነገር ሥልጣን ስለሌለው በፍ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(2) መሠረት ውሳኔውን አጽንተን ይግባኙን ሰርዘናል በማለት ወሰነ።

ይግባኝ ባይ የነበረው ኢንሹራንስ ኩባንያ ይህ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት የሰበር አቤቱታውን ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቀረበ። የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያረጋግጣሉ በማለት ያላቀረባቸው ምክንያቶችም:-

ሀ. በማንኛውም ተከራካሪ ወገን ክርክር ሳይነሳ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት የፍ/ቤቱን የሥረነገር ሥልጣን መኖር አለመኖር አንስቶ በጭብጥነት በመያዝ መወሰኑ የሥነሥርዓት ግድፈት መፈፀሙን ያሳያል፤

ለ. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ተቀብሎ ውሳኔ የሰጠው በክርክሩ ከተጠየቀው የገንዘብ መጠን አንፃር ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሆኑና በፌዴራሉ ሕገመንግሥት በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን በመተካት ስለሆነ እንጅ ጉዳዩ የፌዴራል ፍ/ቤት ሥልጣን ነው። የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ውሳኔ ከመስጠት በክልሉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ያቋቋመው አዋጅ ቁጥር 322/95 ስለሚከለክለው ይግባኙ በክልሉ ለተቋቁመው ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረቡ ሕጉን የተከተለ ሆኖ ሳለ ውድቅ መደረጉ ሕጉን የተከተለ አይደለም፤

የሚሉ ናቸው።

## 2. የሰበር ችሎቱ ውሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሮ በአሶሳ ዞን የተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት አጽንቶታል። የሰበር ችሎቱ ውሳኔውን ለመስጠት ያበቁትን ምክንያቶች ሲያትትም በመጀመሪያ ክርክሩ የተነሳው የክልሉ ነዋሪ በሆኑ ሁለት ግለሰቦች መካከል እንደሆነ ጠቅሶ የኢንሹራንስ ኩባንያው ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ስለተፈቀደለት ጣልቃ ገቢው በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር እንዲወድቅ ሊያደርገው ይችላል ወይ? የሚለውን ጥያቄ አንስቶ መልሱን ሳይሰጥ በማለፍ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸውን ሁለት ምክንያቶች በዝርዝር ተንትኗል።

እነርሱም:-

1. ክሱም ሆነ የይግባኝ አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን፣ ይግባኙን ተመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚያችለው የሥረነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ በተከራካሪ ወገኖች በጉዳዩ ላይ ክርክር

ባይቀርብበትም ከፍርድ በፊት በማንኛውም ጊዜ በራሱ አነሳሽነት አንስቶ መዝገቡን መዝጋት እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በአንቀጽ 9፣231፣207፣211 እና 228 የተደነገገ በመሆኑ ይህን ነጥብ በተመለከተ ፍ/ቤቱ ስህተት ፈጽሟል ተብሎ በአቤቱታ አቅራቢው የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤

2. የሰበር አመልካች ይግባኙ በአሶሳ ዞን ለተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረብ ይገባዋል በማለት ላቀረበው ክርክር መሠረት ያደረገው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን በተወሰኑ ክልሎች ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 322/95 ነው፡፡ የዚህ አዋጅ ይዘት እንደሚያስረዳው ደግሞ ክርክር የተነሳበትን የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልልን ጨምሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተቋቋመባቸው በአምስቱም ክልሎች የሚገኙ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ቀደም ሲል በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 80(2) የፌዴራል ጉዳዩችን ለማየት በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ስለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆነው በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣናቸው ጉዳዮችን ለማየትና ለማስተናገድ ተሰጥቷቸው የነበረው ሥልጣን ቀሪ መሆኑን የሚያሳይ እንጅ የእነዚህ ክልሎች ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ሥልጣን ያዩትን የፌዴራል ጉዳይ በይግባኝ ተቀብለው ለማየት ያላቸውን ሥልጣን ያስቀረ አይደለም፡፡በዚህም መሠረት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚያግደው ምክንያት አልነበረም፡፡ እራሱ ባነሳው የክርክር መስመርም ቢሆን ይህንኑ ለመንቀስ ታስቦ እንጅ ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በይዘቱ የፌዴራል ጉዳይ ነው ለማለት ተፈልጎ አይደለም፤የሚሉ ናቸው፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች ላይ በመመሥረትም የሰበር ችሎቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣንን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ የተሰጠ ውሳኔ ነው ካለ በኋላ ይሁን እንጅ ፍ/ቤቱ በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ተወስኖ ነገሩን ሰምቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በሚለው ውሳኔ መገደብ ሲገባው ከዚህ አልፎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንተን ይግባኙን ሰርዘናል ማለቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም በማለት ውሳኔውን ደምድሟል፡፡

3. ትችት

የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረነገር ሥልጣን የለኝም ያለው፡-

1. ክርክሩ በሁለት የአንድ ክልል ነዋሪዎች መካከል የተነሳ የፍትሐብሔር ክርክር መሆኑን፣
2. የኢንሹራንስ ኩባንያው ወደክርክሩ የገባው ጉዳት አድርሷል ለተባለው መኪና የመድን ሽፋን በመስጠቱ ምክንያት በመኪናው ባለቤት እግር ተተክቶ እንጅ የራሱን መብትና ግዴታ በተመለከተ ክስ ያልቀረበበት መሆኑን፣

ከጠቀሰ በኋላ በዚህም ምክንያት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይን የሚመለከት አይደለም በማለት ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ በአመልካች አቤቱታ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያሰኛሉ ተብለው በዝርዝር ከቀረቡለት ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች አንዱን በቀጥታ መልስ የሰጠበት ሲሆን ሁለተኛውን በተመለከተ ግን መልስ የሰጠው በተዘዋዋሪ ነው፡፡ ይኸውም፡-

1. የሥረነገር ሥልጣንን አስመልክቶ በተከራካሪ ወገን ክርክር ሳይነሳ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውስኔ መስጠቱ የሥነሥርዓት ግድፈት ነው በማለት የቀረበውን ክርክር በተመለከተ ሰበር ችሎቱ ክሱም ሆነ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን ወይም ይግባኙን ተመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው የሥረ-ነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ በሌላው ተከራካሪ ወገን ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ክርክር ባይቀርብም ከፍርድ በፊት በማንኛውም ጊዜ በራሱ አነሳሽነትና አንስቶ መዝገቡን መዝጋት እንደሚችል በፍትሐብሔር ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 9፣231፣207፣211 እና 228[2] የተደነገገ በመሆኑ ይህን ነጥብ በተመለከተ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ትክክለኛና በአቤቱታ አቅራቢው በአንደኛ ደረጃ የቀረበውን መቃወሚያ በቀጥታ የመለሰ ውሳኔ ነው፡፡

2. የሰበር አልካች የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ያየው በፌዴራሉ ሕገመንግሥት በተሰጠው የውክልና ሥለጣን መሠረት ጉዳዩ ከያዘው የገንዘብ መጠን አንፃር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን በመተካት እንጅ የጉዳዩ የሥረነገር ሥልጣን የፌዴራል ፍ/ቤት ነው፡፡ ስለዚህም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በክልሉ በአዋጅ ቁጥር 322/95 በተቋቋመበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ ውሳኔ ከመስጠት ይህ አዋጅ ስለሚከለክለው የይግባኝ አቤቱታው በክልሉ ለተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረቡ አግባብ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ የሰበር ችሎቱ፡-

ሀ. የጉዳዩ የሥረ-ነገር ሥልጣን የፌዴራል ወይስ የክልል ነው ከሚለው ጥያቄ ጋር በተያያዘ ክርክሩ የተነሳው የክልሉ ነዋሪ በሆኑ ሁለት ግለሰቦች መካከል በመሆኑና ጣልቃ ገቢው የሰበር አመልካች በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የንግድ ድርጅት መሆኑ ብቻ ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር እንዲወድቅ ሊያደርገው ይችላል ወይ? የሚል ነጥብ በማንሳት ይህ እንዳለ ሆኖ ይልና አዋጅ ቁጥር 322/95 በክልል ፍ/ቤቶች የውክልና ሥልጣን ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ወደ መተንተኑ ይሄዳል፡፡ ይሁን እንጂ ችሎቱ ይህን ጥያቄ በተመለከተ ውሳኔ ሰጥቶ ማለፉ አስፈላጊ ነበር፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ይግባኝ ሰሚው

---

[2] አንቀጽ 228 እዚህ ላይ በችሎቱ የተጠቀሰበት አግባብነት ግን ፈጽሞ ግልጽ አይደለም፡፡

ፍ/ቤትም ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለኝ ወይስ የለኝም የሚለውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛም የሰበር አመልካች ሌላው የውሳኔው መቃወሚያ ነጥብ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ይግባኙን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን እያለው የለኝም ማለቱ ሕጉን የተከተለ አይደለም የሚል በመሆኑ ለጥያቄው መልስ መስጠቱ ተገቢ ነበር፡፡

ሶስተኛውም ጣልቃ መግባት እንደ ዋና ተከራካሪነት ያስቆጥራል ወይም የጣልቃ ገቢው የፌዴራል አካል መሆን የፍ/ቤቱን የሥረ-ነገር ሥልጣን በተመለከተ የሚያመጣው ለውጥ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጥያቄ መመለስና ለመልሱ ምክንያት መስጠት ለበታች ፍ/ቤት ከፍተኛ ትምህርታዊ ጠቀሜታ ከመስጠቱም በላይ ሕግን ለማዳበር ጠቃሚ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ አራተኛ ከታች በዝርዝር የምንመለከተውን ጥያቄ መመለስ ይህን ጥያቄ በተዘዋዋሪ ይመልሰዋል የሚባል እንኳ ቢሆን ይህ ትክክል የሚሆነው የአዋጅ ቁጥር 322/95 ትርጉምን ችሎቱ በተረዳበት መንገድ ብቻ ከተረዳነው ነው፡፡

ምክንያቱም ጉዳዩ የክልል ሥልጣን ነው ወይም የፌዴራል ሥልጣን ነው ብሎ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ጉዳይን በተመለከተ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በይግባኝ ተቀብሎ የማየት ሥልጣኑ ተነስቷል ወይም አልተነሳም ከሚለው ውሳኔ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በአመልካች መብት ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል፡፡ ለምን ቢባል የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያየው የፌዴራል ጉዳይን ነው የሚል ውሳኔ የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ቢሰጥና አዋጅ ቁጥር 322/95 የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ሥልጣኑን አንስቶታል የሚል ውሳኔ ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ቢሰጥ በመጨረሻ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት የወሰነው ያለአግባብ ነው ወደሚል መደምደሚያ ያደርሳል፡፡

ስለዚህም የሰበር ችሎቱ የጉዳዩ የሥረ-ነገር ሥልጣን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንዳለው የክልል ነው ወይስ የፌዴራል ፍ/ቤት ነው የሚለውን ነጥብ አንጠልጥሎ ከመተው ይልቅ መልስ ሰጥቶበት ቢያልፍ ኖሮ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡

ሰ. የሰበር ችሎቱ ከላይ የተመለከትነውን ነጥብ በጥያቄነት ብቻ በማስቀመጥ ቀጥሎ በማንሳት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 322/95ን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች የይግባኙ ጉዳይ በክልሉ ለተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ ይገባዋል ለሚለው አቤቱታው መሠረት ያደረገው ከፍተኛ ፍ/ቤቶችን ስለማደራጀት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 322/95ን እንደሆነ ከጠቀሰ በኋላ የአዋጁ ይዘት ምን እንደሆነ ገልጿል፡፡ በማያያዝም የዚህ የአዋጅ ይዘት እንዳሚያስረዳው ክርክር የተነሳበትን የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልልን ጨምሮ በአምስቱ ክልሎች የሚገኙ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ቀደም ሲል

በፌዴራል ጉዳይ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 80/2 በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ስለከፍተኛ ፍ/ቤት ሆነው በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው ጉዳዮችን ተቀብለው ለማየትና ለማስተናገድ ተሰጥቷቸው የነበረው ሥልጣን ቀሪ መሆኑን የሚያሳይ እንጅ የእነዚህ ክልሎች ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ሥለጣን ያዩትን የፌዴራል ጉዳይ በይግባኝ ተቀብለው ለማየት ያላቸውን ሥልጣን ያስቀረ አይደለም።

በዚህም መሠረት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚያግደው ምክንያት አልነበረም በማለት ከገለፀ በኋላ ይህም በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ሥልጣንን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ የተሰጠ ነው በማለት ደምድሟል በመጀመሪያ ችሎቱ ክርክር የቀረበበት ጉዳይ የሥረ-ነገር ሥልጣን የክልል ፍ/ቤት ነው የሚል እምነት እንዳለው ከውሳኔው ይዘት መገንዘብ የሚቻል ሆኖ ሳለና በዚሁ ላይ ተመስርቶ ጉዳዩን መወሰን እየቻለ የፌዴራል ጉዳይን የሚመለከተውን አዋጅ ይዘት ወደመመልከት ለምን እንደገባ የሚጠቁም አሳማኝ ምክንያት አናገኝም።

ሁለተኛ በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የክልል ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል የውክልና ሥልጣን የተነሳው ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክሎ ለማየት የሚያስችለው የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ እንጅ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ውሳኔ የሰጠበትን የፌደራል ጉዳይ በይግባኝ የማየት ሥልጣኑ አይደለም በማለት የተከበረው የሰበር ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ በምክንያት የተደገፈ ካለመሆኑም ሌላ ከአዋጁም ሆነ ከሕገመንግስቱ ድንጋጌዎች ይህን የሚጠቁም ነገር አናገኝም። የፌዴራሉን ሕገመንግሥት አንቀጽ 80(2) ስንመለከት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከክልል የዳኝነት ሥልጣኑ በተጨማሪ የፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን ይኖረዋል ይላል።

ለዚህ ድንጋጌ መሠረቱ ደግሞ የዚሁ ሕገመንግሥት አንቀጽ 78(2) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሃገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሊወሰን ይችላል ጉዳዩ በዚህ አኳኋን ካልተወሰነ የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ለክልል ፍ/ቤቶች ተሰጥቷል በማለት ያሰፈረው ድንጋጌ ነው። የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 80(5) ደግሞ የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይታያል ይላል።

ከላይ ከተመለከትነው የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 80 (2) የምንገነዘበው የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ጉዳይን በተመለከተ የመጀመሪያ ደረጃና የይግባኝ ሰሚነት ሥልጣን ያለው መሆኑን ነው። ይህ የውክልና የዳኝነት ሥልጣን የሚኖረው ግን ከተሰመረበት የአንቀጽ 78(2) ድንጋጌ እንደምንረዳው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በክልል የፌዴራል ፍ/ቤት እስኪያቋቋም ድረስ ብቻ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የተሰጠው የመጀመሪያ ደረጃና የይግባኝ የዳኝነት የውክልና ሥልጣን ተነጣጥሎ አንዱ ተነስቶ ሌላው ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን የሚጠቁም ድንጋጌ በሕገመንግሥቱ ውስጥ የለም።

የፌዴራል ፍ/ቤትን በክልል የማቋቋም ውሳኔ በምክር ቤቱ እስኪሰጥ ድረስ በክልል ያለው የፌዴራል የዳኝነት ሥልጣን ለክልል ጠ/ፍ/ቤትና ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቷል የሚለው የሕገመንግሥቱ ግልጽ ድንጋጌ ባለበት ሁኔታ የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፌዴራል የውክልና ሥልጣኑ ያየው ጉዳይ በይግባኝ የሚታየው በክልል ጠ/ፍ/ቤት ነው የሚለውን የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ብቻ ነጥሎ በማንበብ በክልሉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከተቋቋመ በኋላም ቢሆን ተፈፃሚ እንደሆነ ይቀጥላል ማለት ፍ/ቤቱ በመቋቋሙ ብቻ ቀሪ የሆነውን የውክልና የዳኝነት ሥልጣን ሕገመንግሥቱ ከደነገገው በተቃራኒ ሁኔታ ሳይኖካ ይቀጥላል እንደማለት ነው።

የአዋጅ ቁጥር 322/95 አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎችን ስንመለከት ደግሞ አንቀጽ 2 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1 ሥር በገለፅናቸው አምስት ክልሎች መቋቋማቸውን ብቻ እንደሚደነግግ እንረዳለን። አንቀጽ 3 ደግሞ በአምስቱ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶችን ያቋቋመው አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 78(2) በተሰጣቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን መሠረት በተጠቀሱት ክልሎች የክልል ጠ/ፍ/ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት ፍ/ቤት ታይተው ይወሰናሉ ይላል። አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በክልል ጠ/ፍ/ቤቶች መታየት የተጀመሩ ጉዳዮች ደግሞ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲያያቸው ወክልና የተሰጠው ጉዳዮች ወይም የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ውሳኔ ሰጥቶባቸው በይግባኝ የቀረቡ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ።

አዋጁ የሚለውም በየትኛውም አይነት የሥልጣን ሁኔታ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችም ቢሆኑ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ ከሆነ በክልሉ አዲስ ወደ ተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዛወር ሳያስፈልጋቸው በልዩ ሁኔታ በዚያው ይጠናቀቃሉ ነው። ይህ ማለት ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃም ይሁን በይግባኝ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ይቀርብ የነበረ የፌዴራል ጉዳይ አዋጁ ከወጣ በኋላ የሚቀርበው በአዋጁ ለተቋቋመው የፌዴራል ከእተኛ ፍ/ቤት እንጂ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አይደለም ማለት ነው።

እንዲያውም የአዋጁ አንቀጽ 3(2) አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በክልል ጠ/ፍ/ቤት መታየት የተጀመረ የፌዴራል ጉዳይንም ቢሆን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት (በክልሉ በተቋቋመው) እንዲታዩ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሊወስን እንደሚችልም ይደነግጋል።

ከተመለከትናቸው የፌዴራሉ ሕገመንግሥትም ሆነ በአምስት ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ፍ/ቤቶቹ በተቋቋሙባቸው ክልሎች የሚገኙ የክልል ጠ/ፍ/ቤቶች በውክልና ተሰጥቷቸው የነበረው የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ የይግባኝ የፌዴራል ጉዳይ ሥልጣን መነሳቱን እንጂ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን ለሁለት ተከፍሎ የይግባኝ ሥልጣኑ በክልል ጠ/ፍ/ቤት በውክልና እንደተያዘ

እንደሚቀጥልና የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣኑ ግን ከክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ውክልናው ተነስቶ በክልሉ ለተቋቋመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደተሰጠው አይደለም፡፡

በዚህም ምክንያት የተከበረው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 322/95 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች መቋቋም ያስቀረው የክልል ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክሎ በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ጉዳዮችን ማየትን እንጂ የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በውክልና ሥልጣናቸው አይተው የወሰኑትን ጉዳይ በይግባኝ ተቀብሎ የማየት የውክልና ሥልጣኑን አይደለም በማለት የሰጠው ድምዳሜ ከሕጉ ጋር የተጣጣመ ሆኖ አይታይም፡፡

## ማጠቃለያ

የተከበረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በዚህ ትችት በተመለከትነው ጉዳይ አንዳንዶቹ ያነሳቸው ነጥቦችና የደረሰባቸው ድምዳሜዎች ተገቢና ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆንም፡-

1. ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ ውሳኔ የሰጠበትንና የሰበር አቤቱታ አቅራቢውም አንዱ የመቃወሚያው መሠረት አድርጐ ያነሳውን ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የፌዴራል ነው ወይስ የክልል ፍ/ቤት የሚል ነጥብ ዝርዝር ምክንያት ሰጥቶ መወሰን ሲገባው በጥያቄነት ብቻ አንስቶ ወደ ሌላ ነጥብ ማለፉ የውሳኔውን ግልጽነት፣ አስተማሪነትና ጥንካሬ የቀነሰ ጉድለት ሆኖ ይታያል፡፡
2. የችሎቱ እምነት ጉዳዩ የክልል ሥልጣን እንጅ የፌዴራል ሥልጣን አይደለም ወደሚል ድምዳሜ ያዘነበለ እንደሚመስል ከውሳኔው አጠቃላይ ይዘትና በውሳኔው ውስጥ ከተጠቀሱ አንዳንድ ሐረጐች መገንዘብ የሚቻል ሆኖ ሳለ የፌዴራል ፍ/ቤትንና የክልል ፍ/ቤትን የውክልና ሥልጣን ግንኙነት የሚመለከተውን አዋጅ ቁጥር 322/95 ይዘት ወደመተንተን ለምን እንደገባ ግልጽ አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ የክልል ሥልጣን ነው ለተባለ ጉዳይ የፌዴራል ፍ/ቤትንና የክልል ፍ/ቤት የውክልና ሥልጣንን የሚመለከት አዋጅ ይዘት መዘርዘር ያለው አግባብነት ጥያቄ እንዳለ ሆኖ ሕጉን አስመልክቶ የተደረሰበት ድምዳሜም ትክክል ሆኖ አይታይም፡፡

ምክንያቱም፡-

ሀ. በመጀመሪያ አዋጁ የክልል ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል የውክልና ሥልጣን ቀሪ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ተክቶ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያየውን ጉዳይ በተመለከተ እንጅ የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፌዴራል የውክልና ሥልጣኑ አይቶ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ ማየትን አይደለም በማለት የተሰጠው ድምዳሜ ምንም ምክንያት

ያልተሰጠበትና በየትኛው የሕግ ድንጋጌ መሠረት ወደዚህ ድምዳሜ እንደተደረሰ የተጠቀሰ ነገር የለም።

ለ. ከፌዴራሉ ሕገመንግሥትም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶችን በአምስት ክልሎች ካቋቋመው አዋጅ አግባብ ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ስንመለከተውም በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መቋቋም የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በውክልና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ሥልጣን የሆኑ ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን ሥልጣናቸውን ባይነካም የክልል ጠ/ፍ/ቤቶች በውክልና ተሰጥቷቸው የነበረው የፌዴራል ጉዳይን በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ የማየት የውክልና ሥልጣን ቀሪ ያደረገ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሆኖ ሳለ የሰበር ችሎቱ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል የዳኝነት የውክልና ሥልጣን በአዋጁ ቀሪ የሆነው ከፍተኛ ፍ/ቤቱን ተክቶ በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣኑ ብቻ ነው በማለት የሰጠው ድምዳሜ ከሕጉ ጋር የተጣጣመ ሆኖ አይታይም።